# ሙስናን የመታገል ጉዳይ፤ ቀዳሚ አጀንዳ ሆኖ ይቀጥላል!

## ኢዛና ዘመንፈስ 10-12-17

ኪራይ ሰብሳቢነት በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ እያሳደረ ስላለው አሉታዊ ተፅእኖ ጉዳይ መንግስት ራሱም በየአጋጣሚው ከመናገር ቦዝኖ አያውቅም፡፡ እናም ችግሩ ሀገሪቷ የምትመራበትን ፌደራላዊ ስርዓት ላልተጠበቀ የቅልበሳ አደጋ ሊያጋልጥ የሚችል እየሆነ ስለመምጣቱ እንደ ህብረተሰብ የጋራ ግንዛቤ ላይ ከደረስን ዓመታት እንደተቆጠሩም ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡ ከዚህ የተነሳም የፌደራሉ መንግስት ሙስናን አምርሮ የመታገል ጉዳይ ለነገ የማይባል አንገብጋቢ ሀገራዊ አጀንዳ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚገባ በማመኑ ምክንያት ነው ከቀርብ ጊዜ ወዲህ ጥናት ላይ የተመሰረተ የፀረ ኪራይ ሰብሳቢነት እርምጃ መውሰድ የጀመረውም፡፡

በዚህ መሰረትም ካለፈው 2009 ዓ.ም መገባደጃ ጀምሮ፤ የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን፤ ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ጋር በመተባበር ጥቂት የማይባሉ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎችና እንዲሁም ደግሞ የግል ባለሀብቶችን ጭምር በከባድ የሙስና ወንጀል ጠርጥሮ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ሲያደርግ መሰንበቱ የሚዘነጋ ጉዳይ አይሆንም፡፡ ነገር ግን ይህ የፌደራሉ መንግስት የኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚን የህልውናቸው መሰረት አድርገው በሚወስዱት ኃይሎች ላይ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ አምርሮ መነሳቱን ያመላከተው ሰሞነኛ የፀረ ሙስና ትግሉ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ ክፉኛ ያስደነገጣቸው ወገኖች ጥቂት እንዳልሆኑም ይታመናል፡፡ በተለይም ደግሞ ራስን በራስ የማስተዳደር ሕገ መንግስታዊ መብት በተጎናፀፉት የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጫንቃ ላይ ታዝለው የማይገባቸውን ጥቅማ ጥቅም ማጋበስ የለመዱ ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች፤ የፀረ ሙስና እርምጃውን እጅግ በጣም አምርረው እንደሚፈሩት ለመረዳት እንብዛም ምርምር የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡

ምክንያቱም ደግሞ፤ ጥሮ ግሮ ለማትረፍና ድህነትን ለማሸነፍ የሚታትረውን ብዙኃን የህብረተሰብ ክፍል ክፉኛ እያስመረረ የሚገኘው የሙስና ተግባርና አስተሳሰብ፤ ለለየላቸው ጽንፈኛ የፖለቲካ ቡድኖች የህልውና ጉዳይ ተደርጎ እንዲወሰድ የሚያደርገውን ጥቅም

የሚሰጣቸው ስለመሆኑ ደፍሮ መናገር ይቻላልና ነው፡፡ለአብነት ያህልም የፌደራል ስርዓቱን በቀለም አብዮት ለመደርመስና አሁን ያለውን መንግስት አስወግደው መንበረ ስልጣኑን በአቋራጭ ለመቆናጠጥ ያለመ የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴ በማስረግ የሚታወቁት፣ የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ጽንፈኛ አስተሳሰብ አቀንቃኝ ቡድኖች የፀረ ሙስና ትግሉን መጠናከር ለምን እንደጦር ሲፈሩት እንደሚስተዋሉ በምክንያታዊ ማብራሪያ አስደግፈን መመልከት እንችላለን፡፡

ስለዚህም፣ ራሱን “የኦሮሞ ነፃነት ግንባር” እያለ የሚጠራው ኦ.ነግ እና መሰሎቹ የሚታወቁበትን የጠባብ ብሔርተኝነት አባዜ የተጠናወተው የተቃውሞ ፖለቲካዊ አመለካከት የሙጥኝ ማለትን የመረጡትም ሆኑ፣ በተቃራኒው የአስተሳሰብ ፅንፍ ዙሪያ እየተቧደኑ የፌደራሊዝም ስርዓቱን ከማጥላላት ተቆጥበው የማውቁት የትምክህት ኃይሎች ለምን የፀረ ሙስና ትግሉን አምርረው እንደሚፈሩት በምሳሌ አስደግፌ ለማስረዳት ልሞክር፡፡ እንግዲያውስ፣ በኦ.ነ.ግ ፊታውራሪነት የሚንቀሳቀሰውን የጠባብ ብሔርተኞቹ ጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች ጎራ የሚወክሉትም ሆነ፣ እንዲሁም የፌደራል ስርዓቱን በፀረ የሀገር አንድነት የሚፈርጅ አክራሪ አቋም ማራመድን “የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት መገለጫ” አድርገው የሚቆጥሩት የትምክህት ኃይሎች፣ የሚመሳሰሉበት (የሚጋሩት) ነገር ቢኖር፣ ሁለቱም ከኪራይ ሰብሳቢነት ተግባርና አስተሳሰብ ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ጥገኛ ህልውና ያላቸው የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡

ይህን ስልም ደግሞ፣ ሁለቱን ተፃራሪ የፖለቲካዊ አስተሳሰብ ጽንፎች ወክለው ከሀገር ቤት እስከ ባህር ማዶ በተዘረጋ ግልጽና ግልጽ ያልሆነ የተቃውሞ እንቅስቃሴ መረብ አማካኝነት፣ ኢህአዴግ መራሹን መንግስት አስወግደው፣ በትረ ስልጣን ለመጨበጥ የሚያስችላቸውን አቋራጭ መንገድ ለመፍጠር ሲሉ የማይፈነቅሉት የክፋት ድንጋይ እንደማይኖር የመረጋገጡን ያህል፣ በተለይም የሙስና ተግባርና እንዲሁም የብልሹ አሰራር ምንጭ ተደርጎ የሚወሰደውን የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መገለጫ ችግር እንደዋነኛ ህዝቡን ከመንግስት ጋር መቃቃሪያ ብሎም የአመጽ መቀስቀሻ መንገድ ሊጠቀሙበት ይፈልጋሉ ማለታችን እንደሆነ ልብ ይባልልን፡፡

በተጠቃሾቹ ሁለት የተቃውሞ ጎራ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ተቃራኒ ጽንፎች ከሀገር ቤት እስከ ባህር ማዶ በተዘረጋ ግልጽና ግልጽ ያልሆነ (ህቡዕ) መረብ አማካኝነት እየተቀነባበረ

የፌደራል ስርዓቱ ላይ ተደጋጋሚ የቅልበሳ አደጋ የሚቃጣበት መሳፍንታዊ ሴራና ሴራውን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚሞክርበት ፈርጀ ብዙ የፖለቲካ ደባ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የጽንፈኞቹን ዲያስፖራ ተቃዋሚ ቡድኖች አክራሪ አቋም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የሚደግፍ አፍራሽ አመለካከትን የሚያንፀባርቁ ወገኖች፤ እዚሁ አገር ውስጥም ጭምር እጅጉን እየተበራከቱ የመጡበት አውነታ ስለመኖሩም ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡

ይህ ሊሆን የቻለውም ደግሞ፤ ጽንፈኞቹ የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት ፖለቲካዊ አስተሳሰብ አቀንቃኝ ተቃዋሚ ቡድኖች፤ በየፊናቸው የሚታወቁበትን ዓላማ ለማሳካት ሲሉ እንቅልፍ አጥተው በማደርም ጭምር የሚያውጠነጥኑትን መሳፍንታዊ የፖለቲካ ሴራ እንደ ጠቃሚ ነገር ወደ አገር ቤት ነዋሪው ህዝብ ለማዛመት የማይፈነቅሉት የሃኬት ድንጋይ ስለሌለ እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም፡፡ እናም ከዚሁ እያንዳንዷን የሀገራችን ህዝቦች የጋራ ጉዳይ በአክራሪዎቹ ዲያስፖራ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች ጎጠኛ መነፅር ለመመልከት የመፈለግ አደገኛ አዝማሚያ የተነሳ ነው በተለይም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተደጋግሞ እየተስተዋለ ያለው ብሔራዊ ማንነትን መሰረት ባደረገ መፈራረጅ ምክንያት ወደሚቀቀሰቀስ የዕርስ በርስ ግጭት የመግባት ክስተት ጎላ ባለ መልኩ መታየት የጀመረው፡፡ ይልቁንም ደግሞ ከእንደዚህ ዓይነቶቹ የሀገራችንን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በየጥቃቅኑ ምክንያት የዕርስ በርስ ቅራኔ ውስጥ ገብተው በአካባቢያዊ ግጭት እንዲጠመዱና የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ስር የሰደደ ድህነትና ኋላ ቀርነት አምርሮ ስለመታገል አስፈላጊነት ማሰብ እንዲያቆሙም ጭምር ሲባል ከሚውጠነጠኑ መሳፍንታዊ የፖለቲካ ሴራዎች በስተጀርባ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የኪራይ ሰብሳቢ ኃይሎች እጅ ይኖራል ተብሎ የሚታመን ስለመሆኑም በዚህ አጋጣሚ መጠቆም ተገቢ ይመስለኛል፡፡

በግልጽ አነጋገር፤ አሁን አሁን ሲደጋገሙ የሚስተዋሉትን ትርጉም የለሽ አካባቢያዊ የእርስ በርስ ግጭቶች በመቀስቀስ ረገድ የሚጠረጠሩ አንዳንድ የክልላዊ መንግስታት የመስተዳደር ባለድርሻ አካላት የመኖራቸውን ያህል፤ ከእነርሱ በስተጀርባ ጽንፈኞቹ ዲያስፖራ ተቃዋሚ ፖለቲከኞች፤ ከጽንፈኛ ተቃዋሚ ፖለቲከኞቹ በስተጀርባ ደግሞ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዊነትን ከፍታ የማይሹ የውጭ ኃይሎች እንዳሉ ለመረዳት የተለየ ዕውቀት የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡

ስለሆነም፤ በዚህ ዓይነት የጥቅም ትስስር ተቀናጅተው እየተንቀሳቀሱ ሀገራችን የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ አምክነው ለማስቀረት የሚጥሩት የውጪና የውስጥ ኃይሎች ናቸው የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን የህልውናቸው መሰረት አድርገው እስኪቆጥሩት ድረስ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ያላበሱት፡፡

እናም ከዚህ አኳያ፤ መንግስት በኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተግባርና አስተሳሰብ ላይ የበላይነት ለመያዝ የሚያስችለውን የፀረ ሙስና ተግል ትርጉም ባለው ስፋትና ጥልቀት አካሂዶ የሀገራዊ ትርምስ ምንጮችን ማድረቅ ከቻለ፤ በዚያው ልክ ስርዓት አልበኞችን አደብ የሚያስገዛ የተጠያቂነት ሕጋዊ አሰራር መስፈኑ ስለማይቀር ነው ዓለም አቀፋዊው የጽንፈኛ ተቃዋሚዎች መረብ በቅርቡ የተጀመረውን የፀረ ሙስና እርምጃ ለመቀልበስ የለመ ርብርብ ሲያደርግ የሚስተዋለው፡፡ በዚህ መሰረትም፤ ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግና እንዲሁም ደግሞ የኢፌድሪ መንግስት ለወራት በዘለቀ የጥልቅ ተሃድሶ መድረክ አማካኝነት ራሳቸውን በቅጡ ለመመልከት የሞከሩበትን ግምገማ ካካሔዱ በኋላ፤ ለምልዓተ ህዝቡ ይፋ ባደረጉት አቋማቸው፤ አንገብጋቢ መፍትሔ የሚጠይቁ ሀገር አቀፋዊ የጋራ ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ያለመ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ መግለፃቸው አይዘነጋም፡፡ ይሁን እንጂ መንግስትና ገዢው የፖለቲካ ፓርቲ ባካሄዱት የጥልቅ ተሃድሶ መድረክ ላይ ከመቸውም ጊዜ ይልቅ ወደ ውስጣዊ ድክመቶቻቸው ለማየት ስለመቻላቸው ገልጸው፤ በተለይም ለመንግስታዊ ስልጣን የሚሰጠው የተዛባ ትርጉም፤ ሀገሪቷ የተያያዘችውን ፈርጀ ብዙ የዕድገትና ብልጽግና ጉዞ፤ ላልተጠበቀ የቅልበሳ አደጋ ሊያጋልጥ ስለሚችል መታረም ይኖርበታል ወደሚል የጋራ ግንዛቤ መደረሱን ካሳወቁ ጀምሮ፤ ዓለም አቀፋዊው የጽንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እንቅስቃሴ "በፍፁም ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ውስጣዊ ድክመቶቹን ፈትሾ ለህዝብ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ እንዲሰጥ ልንፈቅድለት አይገባም" ከሚል ዕኩይ አቋማቸው በሚመነጭ ዕክል ፈጠራ ምክንያት የጥልቅ ተሐድሶውን ተጨባጭ ውጤት እያቀጨጩት ይገኛሉ፡፡

ከዚህ የተነሳም፤ መንግስት መላው የሀገራችን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከጥልቅ ተሐድሶው መድረክ በኋላ ይጠብቁ የነበረውን ትርጉም ያለው የመፍትሔ እርምጃ ወስዶ እንደ

ህብረተሰብ የጋራ ህልውናችን የተመሰረተባትን ሀገር ወደ ለየለት የትርምስ አደጋ ከማምራት የሚታደግ ተጨባጭ ውጤት ያመጣል የሚል ተስፋችን እምብዛም ሳይሰምር እነሆ ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ ምንም እንኳን ባሳለፍነው 2009 ዓ.ም መጨረሻ ገደማ የፌደራሉ መንግስት የሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ጋር በመተባበር፣ ከባድ የሙስና ወንጀል ፈጽመዋል የሚል የህዝብ ጥቆማ የቀረበባቸውን ኪራይ ሰብሳቢ ተጠርጣሪ ኃይሎች በቁጥጥር ስር የማዋል ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ እንደጀመረ ቢታወቅም፣ ግን ደግሞ እርምጃው ክፉኛ ያስደነገጣቸው የጠባብ ብሔርተኝነትና የትምክህት ፖለቲካዊ አስተሳሰብን በማቀንቀን የሚታወቁት ተቃዋሚ ቡድኖች፣ ከባህር ማዶ እስከ ሀገር ቤት ድረስ በተዘረጋው የዕከል ፈጠራ መረባቸው አማካኝነት፣ እየተመሳጠሩ በሚቀሰቅሱት አካባቢያዊ ግጭትና ትርምስ ምክንያት የፀረ ሙስና ትግሉ መቀዛቀዙን መካድ የሚቻል አይመስለኝም፡፡

ስለዚህም፣ ዓለም አቀፋዊ ስፋትና ጥልቀት ባለው የተጠና ቅንጅት ታግዘው የሚንቀሳቀሱት፣ ጽንፈኞቹ የትምክህትና የጠባብ ብሔርተኝነት አስተሳሰብን በማቀንቀን የሚታወቁ ተቃዋሚ የፖለቲካ ቡድኖች፣ ሀገራዊ የጋራ ህልውናችን ከትርምስ አደጋ ስጋት የጸዳ እንዳይሆን ለማድረግ ሲሉ አሁንም አንቅልፍ አጥተው በማደር ላይ ስለመሆናቸው ደፍሮ መናገር ይቻላል፡፡ እናም እንደኔ እንደኔ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት ሰፍኖ መላው ጥሮ ግሮ አትራፊ ህብረተሰባችን ክፉኛ ሲማረርበት የሚደመጠው የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተግባርና አስተሳሰብ መገለጫ ችግራችን እንዳይቀረፍ የሚሹት ጽንፈኛ ቡድኖች የፀረ ሙስና ትግሉን ሂደት ለመቀልበስ ያለመ ደባቸውን በመፈፀም ረገድ፣ ምናልባትም ከመንግስት ያላሰለሰ ጥረት በላቀ መልኩ እየተረባረቡ ያሉ ሆኖ ነው የሚሰማኝ፡፡ ደግነቱ ግን መንግስት ራሱ ይህን የኔን ስጋት ሳይጋራኝ እንዳልቀረ የሚያመለክት መልካም ዜና ነው ከሰሞኑ ያስደመጠን፡፡

ለዚህ ደግሞ የኢፌድሪ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሙላቱ ተሾመ ባለፈው ሰኞ መስከረም 29 ቀን 2010 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮችንና የፌዴሬሽን ምክር ቤቶችን 3ኛ የሥራ ዘመን በከፈቱበት ንግግራቸው፣ በዘንድሮው የበጀት ዓመት መንግስት የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ከሚያከናውናቸው ሀገራዊ አጀንዳዎች መካከል አንዱ፣ የፀረ ሙስና ትግሉን አጠናክሮ የማስቀጠል ጉዳይ መሆኑን

ስለመግለፃቸው ማስታወስ አያዳግትም፡፡ የክቡር ፕሬዚዳንቱ ንግግር የጋራ ህልውናችን መሰረት የሆነችውን ሀገራችንን የማተራመስ ስትራቴጂ ነድፈው የሚንቀሳቀሱት ስርዓት አልበኞቹ ቡድኖች እንደ ህብረተሰብ የሚያሳስብ ስጋት እየደቀኑብን መሆናቸውን ያገናዘበ የመንግስት እቅድ መኖሩን የሚያመለክት ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ በእርግጥም ደግሞ ኪራይ ሰብሳቢነትን አምርሮ የመታገል ጉዳይ እንደወሳኝ ሀገራዊ አጀንዳ መወሰድ የሚገባው ቁልፍ ነጥብ እንጂ፤ በአንድ ሰሞን ሆይ ሆይታ ብቻ መታለፍ ያለበት ነገር አይደለም፡፡ እንግዲያውስ የኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከፍታ የምንሻ ዜጎች ሁሉ በአዲሱ የ2010 ዓ.ም በጀት ዓመትም ሙሰኞችን አምርረን መታገል እንደሚጠበቅብን እያሳሰብኩ ሐተታዬን እዚህ ላይ አበቃሁ፡፡